


ሦስተኛ ጥራዝ

የያዛቸው የትምህርት አይነቶች


ማውጫ

፩ኛ. የስብከት ዘዴ ከገጽ ፫ - ፶፮

፪ኛ. የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ከገጽ ፶፰ - ፯፭

፫ኛ. የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ከገጽ ፯፯ - ፻፬፩

፬ኛ. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከገጽ ፻፬፫- ፪፻፶፩



፪(ሁለተኛ) ጥራዝ

የያዛቸው የትምህርት ዓይነቶች

ማውጫ

፩. የስብከት ዘዴ ከገጽ ፩- ፲፱

፪. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከገጽ ፳፩- ፶፫

፫. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከገጽ ፶፱- ፩፻፯

የስብከት ዘዴ

ማውጫ ገጽ

መግቢያ ---------- ፩

ክፍል አንድ፡- ኦርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ

፩. ስብከትና የስብከት ታሪክ ---------- ፪

፪. ለሰባኪው የሚያስፈልገው ምንድነው ---------- ፬

፫. የስብከት ዓይነቶች ---------- ፯

፬. ስብከትን በማዘጋጀት ወቅት ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች ---------- ፱

፭. የስብከት ዝግጅት ---------- ፲፭


ክፍል ሁለት፡- ሐዋርያዊ ተልእኮ

፩. ሐዋርያዊና ሐዋርያዊነት ምንድነው ? ---------- ፲፬

፪. የሐዋርያዊነት መሠረቶች ---------- ፲፭

፫. ሐዋርያዊ ማን ነው ---------- ፲፯

፬. ሐዋርያ ሊጠነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ---------- ፲፯ – ፲፱



በስመአብ ወወልደ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን

መግቢያ

ስብከተ ወንጌል የቅድስት ቤተክርስቲያን ዋናው ተልእኮ እና አገልግሎት ነው። ምክንያቱም የቅድስት ቤተክርስቲያን ዋናው ተልእኮ ያላመኑ ሰዎችን ማሳመን ያመኑ ምእመናንን ማጽናት እና አምነው የነበሩ ነገር ግን በተለያየ ምክንያት ከቢተክርስቲያን የራቁትን ማቅረብ ሲሆን ይህ በየዘመኑ የሚፈጸመው ቃለ እግዚአብሔር በማስተማር ነው። ስለዚህ ስብከተ ወንጌል የቤተክርስቲያን ዋነኛውና ተቀዳሚው ተልእኮዋ ነው። ከዚህ አንጻር ታዲያ ስለስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሚሰማሩ ሰባኪያን ይህንን ተልእኮ አንጻር በአግባቡ ማሰልጠንና ብቁ አድርጎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የዚህ የስብከት ዘዴ ትምህርት አላማም ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሚሰማሩ ሰባኪያንን ለአገልግሎቱ ብቁ ይሆኑ ዘንድ ስለ ስብከተ ወንጌል አኅልግሎት ግንዛቤ ለመስጠት የተዘጋጀ መድብል ነው።

ይህ መድብል በውስጡ የስብከት ዘዴና ሐዋርያዊ ተልእኮ የሚሉ ክፍሎች የያዘ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል

አንድ ሰባኪ ስብከትን እንዴት ማዘጋጀት እና ማቅረብ እንዳለበት ሰባኪ ወንጌል ሆኖ ሲያገለግል ለአገልግሎቱ መሳካት የሚያስፈልጉት ነገሮች ምን እንደሆኑ የሚዘረዝርና የሚያስተምር ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የሰባኪ ወንጌሉን ህይወትና አቋም የሚመለከቱ ጉዳዩች የተዘረዘሩበት ክፍል ነው።

እነዚህ ሁለት ክፍሎች አስፈላጊ እና ወሳኝ ቢሆኑም ይህንን ትምህርት በማስተማር ወቅት የመጀመሪያው ክፍል ትልቅ ትኩረት ሊደረግ ይገባዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለተኛውን ክፍል ሰልጣኞች በራሳቸው አንብበው እንዲረዱት በመጠቀም ሀሳብን ማስጨበጥ የሚቻል በመሆኑ ነው። የመጀመሪያው ክፍል ልምምድ የሚጠይቅ በመሆኑ አሰልጣኞች በዚህ ክፍል ላይ ትኩረት በማድረግ የተሰጡ ልምምዶችን ሰልጣኞች እንዲለማመዱ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ክፍል አንድ፡ አርቶዶክሳዊ የስብከት ዘዴ

1. ስብከትና የስብከት ታሪክ

ሀ. የስብከት ትርጉም

ስብከት የሚለው ቃል ሰበከ አስተማረ፣ አዋጀ ነገረ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ነው።

የቤተክርስቲያን ዋናው ተልዕኮዋ ሰዎችን ካለማመን ወደ ማመን ማምጣት፣ ያመኑትን ደግሞ በእምነታቸው ማጽናት ነውና። ስብከት የቤተክርስቲያን ትልቁ የአገልግሎት ክፍል ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድና አሳብ፣ በሰውም ላይ ያለው በጐ ዓላማ ወደ ሰው ልብ የሚደርሰው፣ ሃይማኖት የሚስፋፋብትና የሚተላለፍበት ከፍተኛው መሳሪያ ስብከት ብቻ ነው። /1ቆሮ 1:21/

ከዚህ ጽንሰ ሐሳብ በመነሳት ስብከት

1. የአምልኮ ክፍል ነው
   እግዚአብሔር የምናመልከው አምላካችን ነው። ማምለክ፣ ማመንና መዳን መሰረቱ መስማቱ ነው። ሮሜ. 10:10ጠ17
2. ትዕዛዘ እግዚአብሔር ነው
   ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን የጠራበትና የመረጠበት ዓላማና የመጨረሻው ትእዛዝ ስብከት ነው። ማር 16:15። ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደሆነ እንመሰክር ዘንድ አዘዘን። ሐዋ.10:42
3. ስለ እግዚአብሔር የምንመሰክርበት ነው
   ምስክርነት ማለት ያዩትንና የሰሙትን እውነት ያላዩ እንዲያዩ፣ ያልሰሙም እንዲሰሙና እውነት የሆነውን ነገር እንዲያረጋግጡ በሆነው ሁሉ መናገርና መግለጽ ነው። ጌታም ስለ ምስክርነቱ አስተምሮል። /ዩሐ. 1:6፣ 1ዩሐ 1:1፣ ማቴ 10:32/
4. የእግዚአብሔር መንግሥት የምትገለጥበት ነው
   መንግሥተ ሰማያትም የምትገለጠው /የመትሰበከው/ በስብከት ብቻ ነው። /ማር 1:21/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን በጨለማ የምንገራችሁን በብርሃን ተናገሩ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ስበኩ በማለት አዟቸዋል።

ለ. የስብከት ታሪክ፡

ስብከት የራሱ የሆነ ታሪካዊ ሂደት አለው ከቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ከታሪክ መዛግብት እንደምንረዳው የስብከት አጀማመርና ዕድገት አለው።

1. ዓለመ መላእክት፡ መላዕክት በተፈጠሩበት በመጀመሪያው ቀን የመላእክት አለቃ የነበረው ሳጥናኤል የተፈጠረበትን ዓላማ በመሳት ክህደትንና ሐሰተኛነትን ከራሱ አፍልቆ እኔ ፈጠርኳችሁ ባለ ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል ንቁም በበህላዌን እስከ ንረክበ ለአምላክነ በማለት መላእክትን አጽናንቷል አረጋግቷል። ስብከት ማለት ማጽናናት ማረጋጋት ማለት ነውና። ምላ. 1:35፣ ኢሳ. 40:1 መጋቤ ሐዲስ የሚለው ስያሜም ከዚህ የሚጀምር ነው።
2. ሕገ ልቡና፡ ሕገ ልቡና የምንለው ከአዳም እስከ ሙሴ ያለው ዘመን አበው ነው። በዚህ ጊዜ ሄኖክ ኃጢያተኞች ከኃጢያታቸው እንዲመለሱ፣ ኖኅም ሊመጣ ካለው የጥፋት ውሃ እንዲያመልጡ፣ አብርሃም የዑር ምድር ሰዎች ከጣኦት አምልኮ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ስብከዋል። ይሁዳ 14፣ 2ጴጥ 2:5፣ ኩፋሌ 11:14።
3. ሕገ ኦሪት ከሙሴ ጀምሮ እስከ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዩሐንስ ያለው ዘመን በአጠ ቃላይ ዘመነ ኦሪት ይባላል። በዚህ ዘመን የስብከት አገልግሎት ያደገበት መጽሐፋዊ

የሆኑት እንደሆነ እንገነዘባለን። ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እያሉ በቃልም በጽሑፍም ሰብከዋል።

4. ዘመነ ወንጌል

ዘመነ ወንጌል የምንለው የአዲስ ኪዳንን ዘመን ነው። የዘመነ ወንጌል የመጀመሪያው በር ከፋችና መንገድ ጠራጊ ሰባኪ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ነው። /ማቴ 23:35/ መንግስተ ሰማያት ተቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ክርስቶስንና ክርስትናን ያስተዋወቀ ዮሐንስ ነውና። /ማቴ 3:2/

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከተማ በገጠር በተራራ በባሕር ዳርቻ በስርግና በለቅሶ ቤት በየመንገዱ ሁሉ ከሥፍራ ሥፍራ እየተንቀሳቀሰ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል እየሰበከና ዘመኑ ተፈጸመ፣ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ፣ ኢየሱስ በምኩራባቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ ... በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር ከእርሱ ዕርገት በኃላም ቅዱሳን ሐዋርያት በተለይም የተስፋውን ቃል ከተቀበለ በኃላ

- በአይሁድ ምኩራብ
- በጣአታት ቤቶች
- በፍልስፍና ዐደባባይ
- በለቅሶ ቤት ከተጋድሉ ጋር ሰብከዋል።

ከሐዋርያትም በኃላም የእነርሱ ተከታዮች ሐዋርያውያን አበው፣ በዘመነ ሰማዕታት፣ በዘመነ ሊቃውንትም ሰብከተ ወንጌልን

- በቃል
- በጽሑፍ
- በትርጉም ሥራ
- በድንቃድንቅ ተአምራት
- በክርስቲያኖች የአንድነትና የፍቅር ኑሮ
- በተለያዩ ተጋድሉዎች ሊሰፋፋ ችሏል።

ሐ. ሰብከተ ወንጌል በኢትዮጵያ፡

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በጃንደረባው አማካይነት እንደሆነ የታወቀ እውነት ነው። ጃንደረባው አምኖና ተጠምቆ ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኃላ የክርስትናን ዜና ለኢትዮጵያውያን አብሥሯል።

ጃንደረባው ባከሰ በ35 ዓ.ም ያስገባውን የምሥራች ወንጌል ሰብከት ያቀጣጠለውን ወደ ብሔራዊነት ደረጃ ከፍ ያደረገው የሥነ ጽሑፍ ይዘት የፊደል ቅርጽና ሆሄ አሁን ባለበት ደረጃ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደረገው የቅዱስ ፍሬምናጦስ ከነገሥታቱ ጋር በመሆን ነው። እስከ ዩዲት መነግሥት ድረስ ነገሥታቱ፣ ዘጠኙ ቅዱሳን፣ ቅዱስ ያሬድ መጻሕፍትን በመቀርጉም ስከተ ወንጌልና የምንኩስና ሕይወት እንዲሰፋፋ አድርገዋል።

ከዮዲት መነግሥት በኃላ ደብዝዞ የነበረው የሰብከተ ወንጌል እንቅስቃሴ ትንሣኤ ያገኘው ወርቃማው ከሚባለው 11ኛው እስከ 14ኛው በነበረው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ ዘመን፡

- በዮዲት ምክንያት ወደ አረማዊነት ሂዶ የነበረው ምዕመን ወደ ክርስትና ተመልሷል።
- በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል።
- ብዙ ገዳማት ተገድመዋል ዋልድባ፣ወላይታ አቡነ ተክለሃይማኖት፣ጦመ ግራርያ፣ምሀር እየሱስ(ጉራጌ)፣እሰቦት፣ዝቋላ(የዝዋይ ገዳማት)
- ሥርዓተ ምንኩስና ተስፋፍቷል

- ብዙ የአብነት ትምህርት ቤቶች ተከፍተው የሰብከተ ወንጌል ማዕከል በመሆን አገልግለዋል። ምሳሌ ሐይቅ እስጢፋኖስ
- ብዙ ቅዱሳንና አያሌ ሊቃውንት የተገኙበት ዘመን ነው። ለምሳሌ ከቅዱሳን አቡነ ተክለሃይማኖት ፣አቡነ ዜና ማርቆስ፣አባ ላሙኤል ዘዋልድባ እና ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ ከሊቃውንት ለምሳሌ አባጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣እጹ ዘርዐ ያዕቆብ እና አባ ጽጌ ድንግል ይገኙበታል።
- የመጻሕፍት ትርጉም ሥራ ተከናውኖበታል።
- ድንቅ የሆነው የቅዱስ ላሊበላ ሥራዎች የዚህ ዘመን ውጤቶች ናቸው።

የግራኝ መሐመድ መነሣት ለሰብከተ ወንጌል፣ ለክርስትና መዳከም ዋና ምክንያት ነው። በዚህ ዘመን ከዮዲት በኃላም ከድርቡሾች፣ ከእንግሊዞችና ከጣሊያኖች ወረራ ጋር ሊነጻጸር የማይችል ጥፋት በቤተክርስቲያን እና በሀገሪቱ ደርሷል። አሻራዎቹም 500 ዘመናት ተሻግረው ዛሬም ድረስ ተጽእኖ እንደፈጠሩ ነው።

ለምሳሌ፡

- ሙስሊምና ክርስቲያን መጋባት
- የቤተ ክህነት የሙያ ደረጃ ዝቅ ማለት
- የአረማዊነት ባሕል መቀላቀል
- ያለ ንስሐ አባት መኖር
- ያለ ምክረ ካህን፣ ያለ ሥርዓተ ተክሊል መጋባት
- ብዙ ሚስቶች ማግባት፣ ዕቁባት መስቀመጥ

2. ለሰባኪው የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ነቢያት ወደ ሕዝቡ ከመላካቸው በፊት ስለሚሄዱበት ጉዳይ በሕልም በራዕይ በተለያዩ መንገዶች ተገልጦ እግዚአብሔር ያነጋግራቸውና ተልዕኳቸውን ይፈጽሙ ነበር። ሐዋርያትም ወደ ዓለም የምሥራቹን ወንጌል ይዘው ከመሄዳቸው በፊት ሦስት ዓመት ተምረዋል።

ሀ. ትምህርት

ይህም ማለት ሰባኪው በየትኛውም ደረጃና ሁኔታ ውስጥ ቢሆን በሁሉም መንገዱ ቃለ እግዚአብሔር የተማረ፣ ለመማር የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል። እንደሚባለው ሰባኪ ሙሉ የሆነ ነገር ከሌለው የምእመናን ልብ ማርከት አይችልም፣ የሚናገረው ይጠፋዋል። ስለዚህ ከሌሎች መምህራን፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት፣ ከምቹ አጋጣሚዎች ወዘተ መማር አለበት።

ለ. ለክርስቲያናዊ ሕይወት

የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያገለግል፣ ክርስቶስ የሰበከውን ቅዱስ ወንጌል የሚናገር አባቶች በቆሙበት የሰብከት ሰገነት የሚቆምና ምእመናንን ወደ እግዚአብሔር የሚጠራ ሰባኪ ሃይማኖቱ የቀና፣ ስነምግባሩ የተስተካከለ መሆን ይጠበቅበታል።

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ሰባኪው፡

- የሚጣፍጥ ጨው
- የሚያበራ መብራት
- መልካም መዓዛ ያለው መሆን አለበት።

ከእውቀት ይልቅ ተግባር ይሰብካልና። በመድረክ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ስብከት እየሰበኩ ከመድረክ ጀርባ ተራ ምእመን የማይደፈረውን የድፍረት ኃጢአት የሚያደርግና በወረደ የክርስትና ሕይወት የሚኖር ከሆነ እርሱም ትምህርቱም ይናቃል። በሁለም ነገር አርአያ መሆን አለበት፡

- አንደበቱ የታረመ እጹ ንጹህ የሆነ

- በጸምና በጸሎት የሚታወቅ
- የሚውልና የሚያድርበት የተወሰነ እና የሚታወቅ
- አብረውት የሚዉሉ የዘወትር ጓደኞቹ የታወቁ
- በትድስና ህይወቱ የተመሰከረለት
- በፍቅርና በትህትና የሚታወቅ
- ትእግስትን የተላበሰ፣ ጨዋ ቁጥብና አስተዋይ የሚባል
- የምሥጢራት ተሳታፊ የሆነ
- ክፉውን ነገር ሁሉ የተጸየፈ
- ከቡድንተኝነትና ከአድማ ህይወት የተለየ
- ከዘረኝነትና ከጎጠኝነት ስሜት በእጅጉ የራቀ
- ይህን በማድረግ መዝ. 14:1-5 ማቴ 5:12-16 የተጻፈውን መመሪያው ያደርጋል። በተቃራኒው ከተሰለፈ ደግሞ በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም ይሰደባል ተብሎ የስድብና የእርግማን ምልክት ይሆናል። ሮሜ 2:21-24

ሐ. አርአያ ክህነት

ክህነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ሐዋርያትም ወደ አገልግሎት በተሰማሩ ጊዜ በየስፍራው ካህናትን፣ ዲያቆናትን እየሾሙ አገልግሎቱን ወደ ላቀ ደረጃ አድርሰውታል። ሐዋ 6:1-6 ፣ ሐዋ 20:28 ስልጣነ ክህነት ለስብከተ ወንጌል መስፋፋት ትልቅ እና ሰፊ ድርሻ አለው። በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌል ታሪክ በጀንደረባው ቢጀመርም የተሟላ ሆኖ የተፈጸመውና በተግባራዊነት እድገት ያሳየው ከፍሬምናጦስ የክህነት አገልግሎት በኋላ ነው።

የካህናት ትልቁ ሥራ /አገልግሎት/

- መስበክ/ማስተማር/
- ማሳመንና ማጥመቅ
- መመገብ /ምሥጢራትን/
- ምሥጢራትን መፈጸም
- መጠበቅና መከታተል ነው

በስብከተ ወንጌል የተሰማራ ሰው የክህነት አገልግሎት ሊኖረው ይገባል። ያስተማረውን እንዲያጠምቅ ያጠመቀውን ቀድሶ እንዲያቆርብ በንሥሐ አባትነት እንዲያገለግላቸው ነው።

መ. ራስን አለመስበክ

የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፍቃዴን ላደርግ አልሻምና በማለት እንደተናገረው ዮሐ 5፣30 መጥምቀ መለኮት ዮሐንስም /ስለ እራስህ ምን ትላለህ / ብለው ለጠየቁት የሰጠው መልስ /የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ እኔ ነኝ/ ብቻ ነበር ያለው። ዮሐ 1:23 ዮሐንስ የክርስቶስን ፈቃድ እንጂ የራሱን የሚያውቀውን እውነተኛ ታሪኩን እንኳን መናገር አልፈለገም። ሐዋርያው ዮሐንስም በፍጥሞ ደሴት ታስሯል። የታሰረበት ቦታና ምክንያትም እንደ ሮማ ምክር ቤት ከባድ ነበር ነገር ግን ስለእግዚአብሔር ቃል እና ስለእየሱስ ክርስቶስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርኩ በማለት ብቻ ነበር ራዕያቸውን የጻፋው። ራዕይ 1:19

ስለዚህ ሰባኪው

- የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል የሚሰብክ
- ሐዋርያት የሰበኩትን የተጋደሉለትን የሚሰብክ
- ሊታወንት የተረጎሙትንና ያመሰጠሩትን የሚሰብክ
- ሰማዕታት የተለያዩ ጸዋትዎ መከራዎችን የተቀበሉበትን ክርስቶስን የሚሰብክ እንጂ ሰባኪ የእራሱን ነገር መናገር የለበትም።

እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል ዮሐ 3:34 እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን 1ቆሮ 1:23

ሠ. የተሰባኪያንን ስነ ልቦና መረዳት

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተሰባኪያንን ስነልቦና ማወቅ ለስብከተ ወንጌል መስፋፋትና

ዉጤታማነት የላቀ አጽዕኖ አለው።

የሕዝቡን ማንነት ማወቅ ስንል ማህበራዊና፣ ባህላዊ ኑሮአቸውን ስነ ልቦናቸውን የግለሰቡን ማንነት መረዳት ማለት ነው።

ተሰባኪን ወይም አድማጭን የማወቅ ጠቀሜታው

1. የትምህርቱን ዓይነት ለመምረጥ
2. የትምህርቱን ይዘት ለመወሰን
3. የትምህርቱን መጠን ለመወሰን
4. የትምህርቱን ጊዜ ለመወሰን
5. የትምህርቱን አቀራረብ ለመወሰን
6. የምናስተምርበትን ዘዴ ለመምረጥ
7. ከመውቀስና ከማወደስ ለመቆጠብ
8. የተፈለገው ለውጥ እንዲመጣ ለማድረግ
9. ከማጽደቅና ከመኮነን ለመጠበቅ
10. ከመፍረድ ለመዳን
11. በአድማጩ ከመተቸት ለመዳን ናቸው።

ረ. የስብከት ሰዓትን መጠበቅ

ሰበኪው ስብከቱን ውጤታማ ለማድረግ በጊዜ መወሰን ግድ ይለዋል። የሚጠቀምባቸውን ጊዜያት ወስኖ ማክበርና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል። ሰዓት ከረዘመ ስብከቱ ሊንዛዛ እና አሰልቺ ሊሆን ይችላል ምዕመናኑ የመደንዘዝ፣ የመሰላቸት፣ የወሬ የእንቅልፍ ስሜትና አጀርጠ መሄድ ይፈልጋሉ። የስብከቱ ሰዓት ከአጠረም የሚፈለገው መልዕክት አይተላለፍም። የሚሰሙት ይታወክሉ ጥያቄም ይፈጠርባቸዋል።

የስብከት ሰዓት እንደየ ሁኔታው ለመወሰን

1. ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታ፣ ቀዝቃዛ፣ ሞቃታማ፣ ዝናብ የሚበዛበት ፣ ዝናብ ያለወቅቱ የሚዘንብበት ነው ብለ ማረጋገጥ
2. ትምህርቱ የሚሰጠው ሜዳ ላይ፣ ቤተክርስቲያን ውስጥ፣ አዳራሺ ውስጥ ነው ብሎ ማየት
3. ትምህርቱ የሚሰጠው ሚት፣ ከሰዓት፣ ማታ
4. በአካባቢው የተለመደው ምቹ ሰዓት የትኛው ነው
5. ለምን ያህል ሰዓት ሕዝቡ መቆየት ይችላል
6. በአካባቢው ያሉ ሌሎች ተጽዕኖዎች
   - የአሕዛብ
   - የመናፍቃን
   - የፖለቲከኞች
   - የነብረተሰቡ አመለካከት እነዚህ ሁሉ ታሳቢ ሊደረጉ ይገባቸዋል

ሰዓት መጠበቅ እንዴት ይቻላል

1. ሰዓት ወስኖ ከሚመለከታቸው ጋር ተነጋግሮ መጀመር

2. ሰዓቱን በተወሰነ ጊዜ መመልከት
3. ሰዓቱን በመመለከት እያጠቃለለ መሄድ
4. ድንገት የሚፈጠር ካለ ማጽረጥ

ሲ. የስብከት ርዕስ መጠበቅ

ስብከት ርዕሱ ካልተጠበቀ ውጤታማ ሊሆን አይችልም፣ ምእመናኑ የሚጨብጡት ነገር አይኖራቸውም ሰባኪውም ትዝብት ውስጥ ይወድቃል። ርዕስ መጠበቅ የሚሰጠው ጥቅም ትምህርቱ ወጥ እና ያልተደባለቀ ያደርገዋል። ለምሳሌ ስለምሥጢረ ሥላሴ ጀምሮ ሥለ ጸም ማስተማር የለበትም ሰዓትና ርዕስ መጠበቅ የአንድ ሰባኪ መለያዎቹ ናቸው።

የስብከት ዓይነቶች

ይዘትን መሰረት ያደረገ አከፋፈል

የስብከት ዓይነት በይዘታቸው በሦስት ይከፈላሉ እነሱም

1. ትምህርት
   - በእውቀት ላይ የተመሰረተ
   - ተከታታይነት ያለው
   - በግስረጃ የተደገፈ
   - ማብራራትን መተርጎምን ማመስጠርን የሚጠይቅ
2. ትምህርታዊ ስብከት
   - በተምረት የሚሰጥ
   - መነሻው ትምህርት መድረኻው ስብከት የሆነ
   - ግስረጃ በመስጠት ሰውን ወደ ፈጣሪው የሚያቀርብ
   - እውቀትና ህይወት በአንድ ጊዜ የሚያስጨብጥ
3. ስብከት
   - ቀለል ባለ አገላለጽ የሚቀርብ
   - ግስረጻት እና ግሳየት ላይ የሚያተኩር
   - የሰውን ልቦናና አዕምሮ መማረክና መግዛት የሚችል
   - ሁለንተናዊ ስሜቱን የሚቆጣጠር
   - ምዕመናን በሰሩት ኃጢያት ተጸጽተው ንስሀ እንዲገቡ የሚያደርግ
   - የእግዚአብሔርን ቁጣውን፣ ቸርነቱንና ፍቅሩን በአንድ ጊዜ የሚያሰይ

3.2 በትምህርት አቀራረብ ሲታይ ስብከት በሚከተሉት ዘርፎች ይከፈላል

3.2.1 ታሪካዊ፡ ይህ ዘዴ አብዛኛውን ጊዜ በበዓላት ቀን የምናስተምርበት ዘዴ ነው። በየበዓላቱ የእለቱ ስንክሳር ፣ ገድል፣ ድርሳን ይነበባል ይተረካል። ሰባኪውና የስብከቱ ቦታ የአርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንደመሆኑ እነዚህን አስቀድሞ አንብቦና አጥንቶ ለምእመናን ማስተማር ይጠበቅበታል።

3.2.2 ነገረ ኃይማኖት

ከስብከቶች ሁሉ ጠጣርና ከባድ የሚበለው የስብከት ዓይነት ነው ይህንን ትምህርት ለማስተማር ሰባኪው የሚከተሉትን ነጥቦች ማስተዋል ይጠበቅበታል

ሀ. አንድ ነጥብ ላይ ብቻ ማተኮር ለምሳሌ ሀልዎተ እግዚአብሔር ምሥጢረ ሥላሴ

ለ. በሚገባ ማብራራት ሊያስተምር የፈለገውን ነጥብ በሚገባ ማብራራት ይኖርበታል።

የሚያብራራባቸው ዘዴዎችም:

1. ምሳሌዎችን በማንሳት ምሥጢረ ሥላሴን ማስተማር ቢፈልግ በፀሐይ፣ በእሳት፣ በሰው መስሉ ማስተማር
2. ስለ እመቤታችን አማላጂነት፣ የበላኤሰብን ታሪክ በማስታወስ መተረክ
3. ለትምህርት አስረጂ ጥቅሶችን በማንሳት
4. የሊቃውንት ብሂል በመጠቀም

አባቶቻችን በእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያስተማሩበት መንገድ፣ የገለጡበት አባባል የሰጡት ምሳሌ አለ እነዚህን በሚገባ ማብራራት

ሐ. የአባቶቻችን ቃላት መጠቀም፡ ሰባኪው በሚያስተምርበት ሰዓት የማይገቡ ቃለት ተጠቅሞ ምሥጢራትን እንዳያፋልስ የአባቶችን አባባል በሚገባ መጠቀም።

ለምሳሌ፡ ዮሐንስ /ወንጌላዊው/ በተለያዩ ስሞች ይጠራል

- ነባቤ መለኮት
- ታኦሎጉስ
- ወልደ ነጎድጓድ
- አቡቀለምሲስ
- ፍቁረ እግዚእ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

- እመ ብርሃን
- እመ አምላክ
- እመ አዶናይ
- እመ ብርሃን
- እመ ብዙሃን
- ማኅደረ መለኮት
- እግዝዕተ ብዙኃን
- ቅድስተ ቅዱሳን
- ወላዲተ አምላክ እያሉ ጠርተዋታል

የነገረ ሃይማኖት ትምህርት በጣም መርዘም የለበትም። ከረዘመ የሰማዕያኑ አእምሮ ይከብደውና የሚይዘው አይኖረውም። በትምህርቱ መካከልም መናፍቃንን እንዲህ ይላሉ ከማለት ይልቅ የቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ መሰረት በማድረግ የትምህርቱን ጭብጥ ተረድቶ ለጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ትምህርት አዘጋጅቶ ቢያቀርብ መልካም ነው።

3.2.3 ባለ አንድ ሐረግ ስብከት

ባለ አንድ ሐረግ ስብከት የሚባለው ሰባቢው ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሃረግ መዝዞ ያንን ተመርኩዞ የሚሰጥ ትምህርት ነው። ለምሳሌ በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው /ያዕ 1:12/ ብሎ ከተነሣ

- የፈተናን ምንነት
- የፈተናን ዓይነት
- ፈተና የሚመጣባቸው መንገዶች
- ፈተናን እንዴት ማለፍ ይቻላል
- በፈተናው ጸንተው ያለፉ ቅዱሳን ሰዎችን ታሪክ እያነሣ ከህመኑና ከሰው ሕይወት ጋር በማዋሃድ በሰፊው ማስተማር ነው። አንድ ሐረግ ሲሰቡ ድር ይሰበስቡ እንዲሉ።
- ባለብዙ ሐረግ፡ ያለ ርዕስ የሚሰበክ /በትዳሩ ሰዓት፣ በክብረ በዓል/

- ሰምና ወርቅ፡ ማቴ 7፡1-5፣ 2ዜና 25:17 እሚለያስና ኢዮስያስ ያደረጉት ውይይት
- አንጻራዊ፡ ማቴ 7:24፣ ማቴ 24:37

3.2.4 ቅዳሴያዊ ስብከት

ይህ ዓይነት ስብከት በጸም ወቅት በኪዳን የጸሎት ሰዓት፣ በንግስ ጊዜ፣ በሥርዓተ ቅዳሴ መካከል የሚሰጥ ትምህርት ነው። በቤተክርስቲያናችን ዋነኛው የስብከት ዘዴ ነው።

ይህ የስብከት ዘዴ ብዙ ጥቅሞች አሉት።

- በአንድ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ይገኝበታል
- ሀዋሳት በሙሉ ተሳትፎ ያደርጋሉ
- በሁሉም ንዋያተ ቅድሳት ማስተማር ይቻላል
- ከሕጻን እስከ አዋቂ ይታደሙበታል
- በየጊዜው ስለሚሰጥ ትምህርቱ አይረሴ ይሆናል
- ብዙ ታሪኮችንና ትምህርቶችን በአንድ ጊዜ ያቀርባል

ለምሳሌ፡ የቅዳሴው ምንባብ፣ ዜማው /የ3ቱም የዜማ ስልት/ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ፣ /ወንጌል፣ ግብረ ሐዋርያት፣ መልእክት፣ መዝሙረ ዳዊት/ ምስባክ/ የዕለቱ ዜና/ የቅዱሳን ሕይወት/ ስንክሳር እነዚህ ሁሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሕዝበ ክርስቲያንን በሙሉ ማንኑቱን የሚያሳውቁ ስለሆነ ተዋሕዶት ይኖራል።

4. ስብከትን በማዘጋጀት ወቅት ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዩች

4.1 ሕዝብን ማወቅ

ስብከተ ወንጌል ለአንድ ሕዝብ ለማስተማር የሕዝቡን ማንነት ማወቅ የስብከት ወንጌል መመሪያ ነው። አንድ ሰባኪ የህዝቡን ማንነት ሳያውቅ የሚሰጠው የምግባርም ሆነ የቃል ትምህርት ከተሰባኪው ሕይዎት ጋር መዋሐድ አይችልም። ስለዚህ ሰባኪ በተቻለ መጠን የሚያስተምራቸውን / የሚሰብካቸውን ሰዎች ባሕልን ማወቅና ማጥናት ቋንቋን፣ የሃይማኖታዊ ዳራ፣ የተሰባከያኑ የእውቀት ደረጃ፣ የኑሮ መጠናቸውን፣ በአካባቢው ያለ አስተሳሰቦች ወዘተ በተቻለው መጠን ማወቅና መረዳት ይኖርበታል።

4.2 የስብከት ቦታዎችን ማወቅ

ምቹም ቢሆን የስብከት ማእከላዊ ቦታ ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። ከዚህ በተጨማሪ የምሥራቹን ወንጌል ወደ ሕዝብ ጆሮ ለማድረስ ምቹ ቦታዎችንና አጋጣሚዎችን መጠቀም አለበት።

ሀ. ቤተ ክርስቲያን፡

- ዘወትር የሰርክ መርሃ ግብር
- በኪዳን የጸሎት ሰዓት
- በሳምንታዊ መርሃ ግብር
- በወርሃዊ ዓመታዊ በዓላት
- ልዩ ልዩ መርሐ ግብር በማዘጋጀት
- በቀብር ሰዓት

ለ. በሀዘን ቤት፡

በለቅሶ ቤት የሚገኙ ወገኖች ልቡናቸውን የሰበረባቸው፣ መጽናናትን የሚፈልጉ ናቸው። ሃዘንተኞች ሞትንና ሕይወትን፣ ጽድቅንና ኩነኔን፣ የሚያስቡበት ምቹ አጋጣሚ ነው። በዚህ ቦታ ሰባኪው

1. ሃዘንተኞቹን ማጽናናት፡ ዮሐ. 11:25፣ 2ቆሮ. 5:1፣ መዝ 88:48

2. አስተዛዝን ስለ ንስሐ መንገር

ሐ. በሠርግ ቤት

በሠርግ ቤት የሚገኘው ሰው ሁሉ

- ክርስቲያን አይደለም። የተሰበሰበውም ታለ እግዚአብሔር እግራለሁ ብሎ አይደለም። በዚህ ሰዓት ሰባኪው

- አዲስ ተጋቢዎች /የዕለቱ ሙሽሮች/
- ያላገቡትን
- በትዳር ውስጥ ያሉትንም አንድ የሚያደርግ ስብከት መሰበክ ይጠበቅበታል።

1. ሙሽሮች የዛሬ ደስታቸውን ብቻ ሳይሆን የነገውን እንዲመለከቱ፣ ትዳር በፈተና የተከበበ ሕይወት መሆኑን በማሳየት እንዲጸልዩ፣ በእምነት ጸንተው በመወያየት፣ በመግባባት ፣በመተሳሰብና በመረዳዳት እንዲኖሩ፣ በመካከላቸው ማንም ጣልቃ እንዳይገባ መምከር
2. ያላገቡ እስኪያገቡ ድረስ ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸውና ጋብቻቸውን በቤተክርስቲያን በስርዓተ ተከሊል እንዲፈጽሙ መተስቀስና ክብሩን ማሳየት። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ጸታዊ ግንኙነት ኃጢያት፣ ለነገ ትዳርም ጠንቅ እደሆነ እጽንኦት ሰጥቶ ማስተማር።
3. በትዳር ውስጥ ያሉት ጋብቻቸውን በስርዓተ ተከሊል የፈጸሙትን የበለጠ እንዲበረቱ፣ በስርዓተ ተከሊሉ ያልፈጸሙትም ወደ ቅዱስ ቁርባን እንዲመጡና የሚያገኙትን ክብር በማሰየት መስበክ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠርግ ቤት ማስተግሩንና የተገኘው ጥቅም መነገር አለበት ዮሐ. 2፣1ጢ11።

መ. ማረሚያ /መሀኒ/ ቤት

- በመሀኒ ቤት የታሰሩ ሁሉ ወንጀለኞች አይደሉም
- ወንጀል ስርተው፣ ኃጢአት መሆኑን አውቀው የግይጸጸቱ አሉ
- ከታሰሩበት ቦታ ሌላ ወንጀል የሚሰሩ አሉ
- እርስ በእርስ የሚደባደቡ
- ግብረ ሰዶም የሚፈጽሙ አለ

እነዚህ ሁሉ የታሰሩበት ቦታ አንድ ነው በጥበብ ማስተማር የሰባኪው ብልህነት ነው። ወደ እግዚአብሔር መቅረብና መጸለይ እንዳለባቸው፣የወንጀልን አስከፊነት ፣ በስፋት በዝርዝር ማሳወቅ ይገባል ይሄውም

- ለእራስ ሕሊና እና መልካም ስም ስትል
- ለቤተሰብ፣ ለሀገር፣ ለወገን ስትል
- ለቤተክርስቲያን የሚያደርሰውን ጉዳት በመግለጽ

4.3 የኦርቶዶክሳዊ ስብከት ጠባያትን መከተል

የኦርቶዶክሳዊ ስብከት መለያ ጠባያት /ባሕርያት/ ናቸው

1. መጽሐፋዊ፡ ሰስት ነጥቦችን ያካትታል

ሀ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ

- የስብከት መሰረት መጽሐፍ ቅዱስ ነው
- በቤተ ክርስቲያን የሚከናወኑ ተግባራት

ለ. አዋልድ፡ መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉሙ፣ የሚያብራሩ፣ በተግባርም የሚያሳዩ ናቸው አዋልድ መጻሕፍትን መጠቀም

- ሐ. ታሪካው መጻሕፍት፡ የቤተ ክርስቲያን የታሪክ መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ ለሌሎች መጻሕፍት ጋር እዋሀዶ ማቅረብ አለበት።

2. ነገረ መለኮት፡ አራት ነጥቦችን በውስጡ ያካትታል።
   ሀ. ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን
   ለ. መሰረተ እምነት /ዶግማ/
   ሐ. ስርአተ ቤተ ክርስቲያን
   መ. የቤተ ክርስቲያን ትውፊት

3. ስርዓተ ቤተ ክርስቲያን

ሀ. የጸም፣ የጸሎት ስርዓትን መሠረት ያደረገ

ለ. የበዓላት አከባበር ስርዓትን ያደረገ

ሐ. ስርዓተ ቅዳሴን መሠረት ያደረገ

መ. የቤተ ክርስቲያን መዝሙራትን ያካተተ

ሠ. የስግደትና የአገልግሎት ስርዓት መሰረት ያደረገ

4. ማህበራዊ ኑሮን በተመከተ፡

- በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ ክርስቲያኖች ሊኖራቸው ስለሚገባ ግንኙነት ድርሻ ማሳወቅ
- ስለ ክርስቲያን ቤተሰብ አኗኗር በግልጽ ማሳወቅ
- ከሌላው /በእምነት ከማይመስላቸው/ ጋር ስለሚኖራቸው አንድነትና ልዩነት ማሳወቅና መወሰን ቢቻላቸሁስ ከሰው ሁሉ ጋር በሰለም ኑሩ ተብሏልና።
- እለታዊ እና ወቅታዊ ጉዳዩችን በመዳሰስ

5. ጥምረት ያለው

- ነገረ ሃይማኖት እና ስርዓትን
- ሃይማኖትና ስነ ምግባርን
- ሃይማኖትንና ማኅበራዊ ኑሮን በማጣመር ማስተማር ይቻላል።

ለምሳሌ፡ በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ ማቴ. 10:5

- በአሕዛብ ሃይማኖት
- በአሕዛብ ስርዓት
- በአሕዛብ ማኅበራዊ ኑሮ

5. የስብከት ዝግጅት

አንድ ሰባኪ ስብከት ሲያዘጋጅ ስብከቱ ለማን እንደሚሰጥ፡ የት እንደሚሰጥ ካወቀ በኋላ አርቶዶክሳዊ የስብከት ጠባያትን በመከተል ስብከቱን ያዘጋጃል። ስብከት በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው የቃሉ ባለቤት የሆነውን ልዑል እግዚአብሔር በጸሎት መጠየቅ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኔም የቃሉን ደጅ ይክፈልኝ ዘንድ ጸልዩልኝ እንዳለው። ሰባኪው ሁሉ ጊዜ የሚያነብና የሚማር ከሆነ የስብከት ዝግጅትን ቀላል ያደርገዋል። ሆኖም ግን ሰባኪው ማንበብ ትዝ የሚለው ስብከት ለመዘጋጀት ሲል ብቻ ከሆነ የስብከት ዝግጅቱ ጠባብ ይሆናል። በስብከት ዝግጅት ውስጥ ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ማስታወሻ መያዝ ነው። ሰባኪ የሚያስተምረውን ስብከት/ትምህርት በማስታወሻ ደብተሩ ላይ በጥሩ ዝግጅት ካሰፈረ ለማስተማር ቀላል ይሆንለታል። በተለይ በማስታወሻ ላይ ለማስፈር እንዲመች የሚከተለትን የስብከት ክፍሎች ማወቅና መከተል ጠቃሚ ነው።

አንድ ስብከት ስድስት ንዑሳን ዘርፎች /ክፍሎች/ አሉት እነዚህም

1. ርእስ
2. አላማ
3. መግቢያ
4. ዋና ክፍል/ሐተታ/
5. ምክር
6. መደምደሚያ

ሰባኪ ተከታታይ ትምህርት፣ ረጅም ስብከት ለሞር ስብከት ለማዘጋጀት እነዚህን ቅደም ተከተሎች ማወቅ ይጠበቅበታል

5.1 ርዕስ መምረጥ

ርእስ በሚመረጥበት ጊዜ

- የሰዎችን ትኩረት የሚስብ
- የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት የመንቀሳቀስ ኃይል ያለው
- አላማውን በትክክል መግለጽ የሚችል
- አጠር ያለና ግልጽ የሆነ። ርእስ የስብከት ማስታወቂያ ነው።

የርዕስ አመራረጥ መርሆች፡

- በሰማእያኑ ዘንድ አይረሴነት ያላቸው፣ በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉ ቃላት
- ሊተላለፍ የሚገባውን መልእክት ጠቅለል አድርገው የያዙ ቃላት
- ሰባኪው አብራርቶ ለማስተማር አመቺነት ያላቸው
- ምሥጢራትን ያዘለ ቃላት /ሐረጉች/

ርዕስ ከመምረጥ በፊት ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች፡

- ተሰባኪዎች ባሉበት አካባቢ እድሜ፣ እውቀት፣ ጾታ፣ የሚዘውተር አንል ልምዶች፣ ጠ ባዮች፣ እምነቶች ለይቶ ማወቅ።
- የአካባቢው ማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ለይቶ ማወቅ
- እለታዊ፣ ወቅታዊ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ክስተቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት ውስጣዊና ውጫዊ የሌሎች አካላት ተጽእኖዎችን ማጥናት

5.2 የስብከቱን አላማ መለየት

አጠቃላይ የስብከት ዓላማ ምዕመናን ስለእግዚአብሔር ፍቅርና ኃልዎት ስላደረገልንም የማጸን ሥራ ተረድተውና ተገንዝበው እግዚአብሔርን በመውደድ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ከክፋት ወደ ደግነት እንዲመለሱ ማድረግ ቢሆንም በእያንዳንዱ ስብከት ከዚህ አጠቃላይ ዓላማ በመነሳት ትኩረት የሚደረግበት ዝርዝር ዓላማ ሊኖር ይገባል። ዓላማ የስብከት አንጉል ነው ይባላል። ይህም ማለት ስብከቱ ምን መምሰል እንዳለበት፣ በምን መልክ መቅረብ እንዳለበት፣ ምን ምሳሌዎች መነሳት እንዳለባቸው የሚያመላክት ሂደት ስለሆነ ነው። ስለዚህ ሰባኪው ስብከቱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ በዚህ ትምህርት ምዕመኑ ምን እንዲሆኑ ነው የምፈልገው ምን እንዲፈጸሙ ነው የምፈልገው ብሎ በማሰብ ከዚህ አንጻር የትምህርቱ መዋቅር ማስኬድ ይኖርበታል።

- የትምህርቱን ዓላማ በትክክል ማስቀመጥ

አላማ የሚሰጠው ጥቅም

ሀ. የትምህርቱን ዝግጅትና መደምደሚያ መልእክት ይቆጣጠራል

ለ. በትምህርቱ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውና ሊከተቱ የማይገባቸውን ይወስናል

ሐ. የሚዛመዱ እሳቦችን ለመወሰን ይረዳል

መ. የትምህርቱን አላማ ለመፈጸም የሚረዱ ምሳሌዎችን ለመምረጥ

ሠ. ትምህርቱ ግቡን መምታቱን ለመለካት

መ. መደምደሚያ ለመስጠት

የዓላማ አጠቃላይ ግብ ምንድን ነው

1. እውቀት ለማስተላለፍ:
   የአንድምታ ትምህርት፣ ነባረ ሃይማኖት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ነባረ ቅዱሳን
2. መንፈሳዊ ሕይወት ለማስተማር:
   ጸሎት፣ ጾም፣ ንስሐ ሕይወት፣ ቅዱስ ቁርባን
3. የጠባይ ለውጥ ለማምጣት
   - ሰው ከመጥፎ ሥራ እንዲመለስ
   - እኩይ ተግባርን እንዲተው
   - ከኃጢአት ከወንጀል እንዲጠበቅ
4. የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት:

ሰው በአስተሳሰቡ፣ በአመለካከቱ አውንታዊ ለውጥ እንዲያመጣና አቋም እንዲኖረው

1. መግቢያ
   - የአንድ ትምህርት መግቢያ የመማርን ፍላጎት ይቀሰቅሳል
   - ርዕሰ ጉዳዩን የበለጠ ያስተዋውቃል
   - አላማውን በትክክል ይገልጣል
   - የሰማዕያኑን ትኩረት የሚስብና የሚገዛ ይሆናል

ይህ ክፍል ሰባኪው ራሱን ከምዕመናኑ ጋር የሚያለማምድበት፡ የምዕመናኑን ትምህርት አቀባባል ዝግጅት የሚቃኝበት፣ ርዕሱን እና ዓላማውን የሚያስተዋውቅበት ጊዜ ነው። ስለዚህ ሰባኪው ተገቢውን ክርስትያናዊ ሠላምታ ካቀረበ በኋላ ርዕሱን ያስተዋውቃል። በዚህ ወቅት ረጋ ማለትና በጣምም ሳይቆጡ በጣምም ሳቅ ሳያበዙ በተረጋጋ ሁኔታ ርዕሱን ካስተዋወቁ በኋላ ርዕሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከተወሰደ ለርዕሱ መነሻ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማንበብ።

2. የትምህርቱ ዋና ክፍል
   በተከታታይ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች በመግቢያ ከተሰጠው ገለጻና ከተመረጠው ርዕስ አኳያ ከትምህርቱ በእውቀትም በሕይወትም ምን እንደሚጠብቁ መጠየቅና መረጃዎችን ማሰባሰብ።
   - ትምህርቱን ተማሪዎች በሚጀመርት ሁለንተናዊ የማስተማሪያ ዘዴ በግልጽ ቋንቋ ማስተማር።
   - ተማሪዎችን አሳታፊ እንዲያደርግ በጥያቄና መልስ ማስተማር
   - በውይይት በቡድን ከፋፍሎ ማስተማር
   - ከትምህርቱ ጋር የሚሄዱ ምሳሌዎችን መጠቀም
   - አጠር ያለ የቤት ሥራ መስጠት
3. የትምህርት ምክር አስፈላጊነት:
   - ትምህርቱን ከተማሪዎች አለታዊ ኑሮ ጋር አገናዝበን ካላስተማርን ያዘጋጀነው ትምህርት ውጤት አይኖረውም።
   - የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከሕይወት ጋር ካልተዛመደ መንፈሳዊ ድርቀት ያስከትላል።

- ትምህርቱ በይዘቱና በአትራፊው እንከን የሌለው ቢሆን እንኳን የተማሪዎችን ሕይወት ካልለወጡ ትርጉም አይኖረውም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተግባራዊ እንዲሆን

- ከእለት ተእለት ሕይወታቸው ጋር ወቅታዊ ማድረግ
- መሆን ያለባቸውን እንዲሆኑ ትእዛዝ መስጠት
- እግዚአብሔር ከሕዝቡ ምን እንደሚፈልግ በግልጽ በመንገር ትምህርቱን ከሕይወታቸው ጋር ተጨባጭ ማድረግ
- እንዲህ ብታደርጉ መልካም ነው ባታደርጉ ግን ብሎ ምክር መስጠት
- ምን እናድርግ ብለው ራሳቸውን እንዲጠይቁ ማድረግ

4. ለትምህርቱ መደምደሚያ መስጠት:
   - መደምደሚያ መስጠት ትምህርቱን ሙሉና የተጨበጠ ያደርገዋል።
   - የተለያዩ ክፍሎችን ያዋህዳል
   - የትምህርቱን ማእከላዊ አሳብ ያካልላል
   - የትምህርቱን አላማ ያስታውሳል
   - ትምህርቱን ያስተሳስራል

ክፍል ሁለት ሐዋርያዊ ተልዕኮ

ሐዋርያዊና ሐዋርያዊነት ምንድን ነው?

ሐዋርያ የሚለው ቃል ሐረ ሄደ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ነው /የወጣነው/ ሐዋርያ ማለት የተላከ የተመረጠና በእግዚአብሔር የተጠራ፣ ለአገልግሎት የሚፋጠን የቅዱሳንን አሰረ ፍኖት /ፈለግ/ የተከተለ ብቁና ንቁ የሆነ የሐዋርያዊነትን ተልዕኮ በተግባር የሚያሳይ ማለት ነው።

ሐዋርያዊነት፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም በይሁዳ በሰማርያም ሁሉ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክሮች ትሆናላችሁ ሐዋ 1:8 ብሎ ባዘዘው አምላካዊ ቃለመሰረት ሐሩ ወመሐሩ ያለውን በተግባር መፈጸም ነው።

ሐዋርያዊ ተልዕኮ፡ የቤተክርስቲያን ዋና ተልዕኮና ዓላማ ነው። ምክንያቱም እግላክ ሰው የሆነበትና ደሙን ያፈሰሰበት፣ ቤተክርስቲያን በርዳተ መንፈስ ቅዱስ የተመሰረተችበት መሠረታዊ የሆነ ሰዎችን የማዳን ጥሪ ነውና ሰዎችን የድኅነት ባለቤት ለማድረግና ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ በክርስቶስ የሆነውን የምሥራች ወንጌል ድምጽ በማሰማት የቤተክርስቲያን አባል ማድረግ፣ የሰሙትንም ለማጽናት ለመከታተል፣ የጠፉትን ለመፈለግና ለማነጽ የሚደረግ መንፈሳዊ የተጋድሎ ጉዞ ነው። ማር 16:8፣ 16፡ጠ16፣ ዮሐ. 10:16፣ ማቴ 28:19፣ ሉቃ. 19:10።

- ሳምራዊቷ ሴት ያደረገችው ዮሐ. 4:33
- የተበተኑት ቃሉን እየሰበኩ መሆራቸው ዮሐ. 8:4
- አቂላና ጵርስቅላ ለአጵሎስ ያደረጉት አስተዋጽኦ ሐዋ. 18:24

እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩን ሐዋርያዊነት የራሱ የሆነ ደረጃ ቢኖረውም የማንኛውም ክርስቲያን ተልዕኮ መሆኑን ነው። በሰው ፊት ያመነብኝ

እኔም በሰማይ በአባቴ ፊት እመንበታለሁ፣ በሰው ፊት ያፈረብኝን እኔም በሰማይ በአባቴ ፊት አፍርበታለሁ ማቴ 10: 32 የሚለው አምላካዊ ድምጽ ክርስቲያን የሆነውን ሁሉ ይመለከታልና።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማዳረስ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ባላመኑት ትውልዶች መካከል መገኘት፣ ከተወለዱበትና ከሚኖሩበት አካባቢ በመለየት፣ የሚወዱትን ቤተሰብና ሥራ /ሙያ/ በመተው ጊዜው የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት በመቀበል ለማዕትነት በመክፈል ነው።

የሐዋርያዊ ተልዕኮ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ

ሐዋርያ የሚለው ቃል በተግባር የተገለጠው በአዲስ ኪዳን ይሁን እንጂ ሐዋርያነት /አገልግሎትና ተልዕኮው/ ግን ቅድመ ክርስትናም እንደነበረ የእግዚአብሔር አስትንፋስ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። በአዲስ ኪዳን የተገለጠው በብሉይ ኪዳን በተለያየ መንገድ ሲፈጸም የቆየው ነውና።

የሐዋርያዊነት መሠረቶች

ሐዋርያዊነት ብዙ ዋጋ ያለውና ብዙ ክብር የሚያሰጥ ተልዕኮ ነው። ዋጋ ሊያሰጥ የሚችለውም ሐዋርያዊ /ልዑክ/ ተልዕኮውን በእግባቡ መፈጸም ከቻለ ብቻ ነው።

ሀ. ጽኑ እምነት

በየትኛውም ቦታና ጊዜ፣ የአገልግሎት ሁኔታዎች ታማኝ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። የልዑኩ ግንኙነት ከእግዚአብሔር፣ ከሰውም ጋር ነውና። በአገልግሎት ጊዜ፣ በፈተና ውስጥ መሰዋዕትነትን በመክፈል ለጠራው፣ ለሚያገለግለው ሕዝብና ለአገልግሎቱ ለራሱም ሕሊና ታማኝ መሆን አለበት።

ስለዚህ ሰባኪው በእግዚአብሔር ፍጹም እምነት በራሱም ሕይወት እግዚአብሔር ያደርግልኛል ብሎ መታመንና ተግባራዊ ምላሽ መስጠት አለበት።

ለ. በመንፈስ ቅዱስ መሥራት፡

በሐዋርያው ጳውሎስ የሐዋርያንት ጉዞ ሁሉ የምንረዳው እውነት በመንፈስ ቅዱስ የተሠራ መሆኑ ነው። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚሠሩ ሁሉ ደግሞ የእግዚአብሔርን ልጆች ናቸው የቤተክርስቲያን አገልግሎት መንፈሳዊና ሰማያዊ ነው። ሥራውም መከናወን ያለበት በመንፈስውያን ሰዎች ነው። ለዚህ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡

- ለቅዱሳን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን መላኩ ሐዋ. 2፡15 ሉቃ. 24:54
- በርናባስና ሳውል ለተጠሩበት ሥራ የተለዩት በመንፈስ ቅድስ ነው። ሐዋ. 13:3 ይህም ማለት፡ የሐዋርያት ሥራ የመንፈስ ቅዱስ እንጂ የሰው አለመሆኑን ማመን፣
- ሊከበርበትና ሊመሰገንበት የሚገባው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ብቻ መሆኑን ማመን፣
- የገንዘብ ኃይል፣ የሰው ኃይል፣ ሳይንሳዊና ቴክኖሎጂ እገዛዎች ቢኖሩም ሥራው የእግዚአብሔር ነው፣ የሚሰራውም በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መሪነትና እርዳታ ብቻ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም ብሏልና /ዮሐ. 15:5/።

ሐ. መንፈሳዊነት፡ አንድን የተላከ ሐዋርያ ለተልዕኮው ጉልበትና ኃይል የሚሆነው በልበ ሙሉነትና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በድፍረት መናገር የሚችለው፣ ምእመናን እንዲሆኑ የሚፈልገውን እርሱ ቀድሞ ግድረግ የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህም ማለት የመንፈሳዊነት መታወቂያና መገለጫ የሆኑትን ምሥጢራትን መካፈል ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወት ትልቁ ችግርና ድክመት መንፈሳዊ ሥራዎች መንፈሳዊያን ባልሆኑ ሰዎች መሠራቱ ነው። የኢትያጵያ ቤተክርስቲያን ከለይ እስከ ታች ከትልት እስከ ትንሽ፣ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ያለበት ችግርም ይሄው ጉዳይ ነው። ዛሬ ዛሬ በአገልጋዮች ከማጸናው ይልቅ በአገልጋዩ የሚሰናከለው መብዛቱ የመንፈሳዊነት ጉድለት ነው።

መ ትሕትና እና የኃላፊነት ስሜት፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ ያደረገሁላችሁን አወቃችሁን እናንተ መምህራችን ጌታችን ትሉኛላችሁ፣ መልካም ትላላችሁ እኔ እንዲሁ ነኝና እንግዲህ እኔ መምህራችሁና ጌታችሁ ሰሆን እግራችሁን ካጠብኳችሁ እናንተም እንዲሁ የባልንጀሮቻችሁን እግር ልታጥቡ ይገባል፣ እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንዲሁ አድርጉ ዩሐ. 13:12 በማለት አስተምሯል።

ትህትና ግለት

- ራስን ዝቅ አድርጉ መመልከትና መተበል
- እኔ ለዚህ አገልግሎት ብቁ ነበርኩ ብሎ ራስን መጠየት
- አብርሃም፣ ዳዊት፣ ጳውሎስንና ትህትናቸውን መመልከት
- የትዳሳን አበው የትሕትና ሕይወትና ፈለግ መከተል
- ራስን ክዶ በነገር ሁሉ ክርስቶስን መከተል ማቴ 16:26
- በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብጹዓን ናቸው። ማቴ 5:31 የሚለውን የብጽዕና ቃልኪዳን መመሪያ ማድረግና መጠበት ነው። /ያዕ. 4:6/

1.4 ሐዋርያዊ ግን ነውን?

የእግዚአብሔር ዓላማ በሰው ላይ ሁልጊዜ የፍቅርና የሰለም የድኅንነትና የደስታ፣ የበረከትና የሕይወት፣ የመልካምና የቅድስና ዓላማ ነው። /መኃ 4:2፣ ኤር. 29:11፣ ሕዝ. 18:32፣ ዘጸ 30:15፣ ዩሐ. 3:16።/

እነዚህ ዓላማዎች አሳቦች በሰው ሕይወት ሁሉ ተፈጻሚ እንዲሆኑ እግዚአብሔር በአንድም በሌላም መንገድ ሰዎችን ይጠራል። .

የተጠሩ ሰዎች

- ሙሴ በግ ሲጠብት /ዘጸ. 3:1-10/
- ዳዊት በግ ሲጠብት /1ሳሙ. 16:13/
- ኤልሳዕ በእርሻ ላይ /1ነገ 19:19/
- አሞጽ የሾላ ፍሬ ሲለቅም /አሞ. 1:1/
- እነ ጴጥሮስ ዓሣ ሲያጠምዱ /ማቴ. 4:18/
- ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ /ሐዋ. 9:1/
- ባኮስ /አቢላክ/ በመንገድ ላይ /ሐዋ 8:26/
- ቶማስ ወደ ሕንድ እንዲሄድ በነጋዴ እማካይነት
- አትናቴዎስ ከሕጻንነት ጨዋታ
- ፍሬምናጦስ በምርኮ ግለ
- አሞብሮስ የሚላኖ አስተዳዳሪ እያለ

የጥሪ መስፈርቶች፡

እግዚአብሔር የጥሪ መስፈርት የሚያደርገው፡ እውቀት፣ ሀብት፣ ሥልጣን ወይም ሌላ ምክንያት አይደለም። 1ቆሮ. 1:26

- የልብ ውስጥ ትንኒት፡ ዳዊት፣ ሙሴ
- መንፈሳዊ ትንዓት፡ እስመ ትንዓተ በ
- ጉጉትና ተነሳሽነት
- ማስተማር ግዴታው መሆኑን የሚያውቅ
- የትም ለመሄድ ዝግጁ የሆነ
- የተለያዩ ፀጋዎች /ሀብታት/ ያለት
- ከሁሉም ነገሮች ነጻ የሆነ
- መስቀሉን በደስታ የሚሸከም

2.3 ሐዋርያ ሊጠነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዩች፡

በሐዋርያነት መስክ የተሰማራ ማንኛውም አገልጋይ ጌታ እንደተናገረው በተራራ ላይ ያለ መብራት ማለት ነው። በሌላ አነጋገር የክርስትና ባንዲራ ነው ምእመናን የሚያጠፉት ጥፋትና እርሱ የሚያጠፋው በሰውም ዘንድ በእግዚአብሔርም ዘንድ በአኩል አይታይም አይመዘንም። የጌታውን ፈቃድ አውቆ እንደ ፈቃዱ የሚሠራና የማይዘጋጅ የዚያ አገልጋይ

ትጣቱ ብዙ ነው ሉቃ.12:47 ተብሎ እንደተነገረው ኃላፊነት ተቀብሎ አውቆ የሚያጠፋ የቅጣቱ መጠን ከባድ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው በመሆኑም ሊነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች::

1. ከንቱ ውዳሴ

ከንቱ ውዳሴ አውቀውትም ሳያውቁትም ብዙዎችን ከዐጋው ዙፋን ያራቆተ፣ ዓላማቸውን ያሳተ፣ አትጣሚቸውን ያሰናከለ ከባድ የሆነ የበጉ ሕሊና ወጥመድና እንቅፋት ነው:: ስለዚህም ነው የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፣ ልናደርገው የሚገበንን አድርገናል በሉ ሉቃ 17:10 በማለት ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን የመከረው::

ከንቱ ውዳሴ የሚመጣባቸው መንገዶች:

ሀ. ከንቱ ውዳሴን መሻት /መፈለግ/

ሐዋርያዊው ከውስጡ መደነቅን፣ መከበርን፣ መወደድን መናፈቅንና/ መፈለግ/ እነዚህን ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮችን በተደጋጋሚ በአንድም በሌላም መንገድ /በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ/ ጥረት ማድረግ::

ለ. ከሌላ አከል: ከሰው ዘንድ በእውነትም ቢሐሰትም ውዳሴና ሙገሳ /አድናቆት/ ሊመሐ ይችላል::

2. ወገንተኝነት: የቆሮንቶስንና የፊልጵስዮስን አብናየተ ክርስተናየናት ናየውኳቸው ከነበሩ ጉዳዮች መካከል አንዱ ወገንተኝነት ነው:: በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን:

- እኔ የጳውሎስ ነኝ
- እኔ የኬፋ ነኝ
- እኔ የአጵሎስ ነኝ የሚል ክፍፍል ነበር 1ቆሮ 3:1ጠ12

ወገንተኝነት በብዙ መንገድ ይገለጣል:

1. የፖለቲካ ወገንተኝነት
2. የቋንቋና ብሄር
3. ከአካባቢው ተወላጆች
4. በቡድን በመሰብሰብ

3. ለምድራዊ ጥቅም ማገልገል:

በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን በእጅጉ የተፈታተናት፣ አንዳንዶችም ያመኑትን ፈጣሪና የታመኑለትንና ያመነቻቸውን ቤተክርስቲያን ከመክዳት አልፈው የጫማ ውስጥ ጠጠርና የጭቃ ውስጥ እሾህ እንዲሆኑባቸው ያደረገው የጥቅም ፍላጎት ነው::

ጌታ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር እና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም ብሎ ቢያስተምርም ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ እስከ መስጠት ያደረሰው ገንዘብ ነው:: በቤተክርስቲያን ታሪክ ለገንዘብ ማገልገል ሲሞኒዝም ይባላል:: /ሐዋ. 8:9ጠ25፣

- ለገንዘብ ብቻ ሲሉ ማገልገል
- ጥሩ ክፍያ ይከፈሉት የሚሉትን ብቻ መርጦ ማገልገል (የነፍስና የሥጋ ብለው ጉባኤያትን እከመከፈል ደርሰዋል)
- ሀብታሞችን ብቻ ማሰባሰብ
- የንስሐ ልጅ መርጦ መያዝ

4. ከፈተናዎች መጠበቅ

ፈተና በተለያዩ መንገድ ይመጣል:: ፈተና ሁሉ ኃጢያት እይደለም የሚፈተን ሰውም በመፈተኑ ብቻ ኃጢአተኛ አይደለም በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው የተባለውም ከዚህ አኳያ ነው:: /ያዕ. 1:12/

ፈተና ከወዴት ሊመጣ ይችላል

1. ከራሱ: የራስ ግላዊ ጠባይ፣ የግል አመለካከትና ፍላጎት፣ ድካምና መሰልቸት ከመንፈሳዊ ሕይወት አለመብሰል፣ በሆነው ሁሉ ተስፋ መቁረጥ፣ ረዳት ማጣት::
2. ከባለ ሥልጣናት: አንዳንድ ባለሥልጣናት ሕዝቡ የሚነቃባቸውና የሚቀሰቀስባቸው፣ በእነርሱም የሚዘምትባቸው መስሎ ሲሰማቸውና ሲታያቸው፣ ሥራችን ይደናቀፋል ብለው ስለሚያስቡ በሰባኪውና በአገልግሎቱ ላይ እንቅፋት መሆናቸው አይቀሬም፣ እየሆነ ያለውም ይሄው ነው::
3. ከወግ አጥባቂነት:
   የመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ጸሐፍት ፈሪሳውያን፣ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ነበሩ::
4. ጥቅማቸው ከተነካባቸው /ሊነካ ይችላል ብለው ከሚያስቡ/ ግለሰቦች:
   ፈሪሳውያን ያለ እግዚአብሔርና ያለ ሙሴ ሕግ ከራሳቸው ሕሊና አመንጭተው የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት ሕገ አውጥተው በሕዝቡ ላይ ጭነው ነበር::
5. ከመናፍቃንና ከአሕዛብ
   በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኞችን ነቢያትና ሐዋርያትን፣ ሊቃውንትና መምህራን ይቃወሙና ከሕዝብና ከመሪዎች ጋር ያጋጩ የነበሩ በውስጥም በውጪም መናፍቃን ነበሩ ለምሳሌ: በኤልያስ፣ በሚክያስ የአገልግሎት ዘመን 1ነገ. 22:13::

ወስብሃት ለእግዚአብሔር